የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
Ginbot 7: Movement for Justice Freedom and Democracy
Tel +44 208 1335670 pr@ginbot7.org

## የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የተመሰረተበትን አንደኛ አመት በሚመለከት የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

እለቱ ግንቦት ሰባት 2001 ዓ.ም ነው። ይህ እለት ለግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ ታላቅ ትርጉም ያለው እለት ነው፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ይህንን እለት የድርጅቱ ስም መጠሪያ ያደረገው ያለምክንያት አይደለም፡፡ ንቅናቄው የቆመበት መሰረት፣ የንቅናቄው መነሻና መድረሻ፣ ህልሙና ራእዩ ከእዚህ በሃገራችን የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ለዘለዓለሙ ሲታወስ ከሚኖረው የ1997ቱ የግንቦት7 ምርጫ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ መሆኑ ነው፡፡ ንቅናቄያችን ስሙን ብቻ ሳይሆን የተመሰረበትን እለት ጭምር ግንቦት 7 2000 ዓ.ም እንዲሆን አድርጓል፡፡ ይህም ያለምክንያት አልነበረም፡፡

የሃገራችን ህዝብ በእዚህ እለት በ1997 ዓ.ም፣ ለመብቱና ለነጻነቱ መከበር ቀናኢ መሆኑን አስመስክሯል፡፡ የዘውግ፣ የሃይማኖትና የቋንቋ ልዩነቶቹ፣ ገዚዎቹ እንደሚመኙት የመከፋፋያና የባርነት እድሜውን ማራዘሚያ ምክንያቶች መሆን እንደማይገባቸው አሳይቷል፡፡ የሃገሪቱ ህዝብ ከዳር እስከ ዳር በጋራ በመነሳት በምርጫ ድምጹ የመረጠውን መንግስት ለመሰየም በአንድነት ተንቅሳቅሷል፡፡ የፖለቲካ ስልጣንን በምርጫ ለፈለገው ሃይል ማስተላለፍ የሚያስችል ብስለት፣ ብቃት፣ እውቀት፣ ባህልና ቁርጠኝነት ያለው ህዝብ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ‹‹የሚበጅህን እኛ ብቻ እናውቅልሃለን›› ለሚሉት ዘረኛ ገዝዎች ‹‹እኔ ለራሴ አውቃለሁ›› የሚለውን የማያሻማ መልእክቱን አስተላልፏል፡፡ በእብሪት በታጀሉ ገዥዎቹ ቅጥፈት እስረኛ ለነበሩና፣ አብላጫው የሃገራችን ደሃ፣ ችግረኛና የዘመናዊ ትምህርት እውቀት ያልደረሰው ህዝብ፣ የዴሞክራሲና የነጻነት ትርጉም ገብቶት ምርጫውን በሙሉ ልቡ አይሳተፍም ብለው ለደመደሙ የውጭ መንግስታት፣ ኢትዮጵያ የተአምር ሃገር፣ ህዝቧም ተአምር ሰሪ መሆኑን 26 ሚሊዮን ጊዜ የተደገመ ተአምር ሰርቶ ያሳያበት እለት ነው፡ ግንቦት 7 1997

የንቅናቄያችንን ስም ግንቦት 7 ብለን ስንነሳ የ1997ቷን ግንቦት 7ን ላንረሳ ‹‹ ግንቦት 7 ብንረሳሽ የሚረሳ ይርሳን›› በማለት በንቅናቄያችን የምስረታ እለት ቃል ኪዳን ገብተን ነው፡፡ የዛሬ አመት በእዚሁ እለት ንቅናቄያችንን ግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ብለን ስናስተዋውቅ፣ በየአመቱ የራሳችንን ድርጅት የምስረታ እለት ብቻ ሳይሆን

ንቅናቄያችን እንዲወለድና እንዲኖር ምክንያት የሆነውን የግንቦት 7 1997 ታላቅ ህዝባዊ ክንዋኔ የምናስታወስበት፣ በእዚያ የምርጫ እለት ህዝብ ሰንቆ የተነሳውን፣ ራሱን ከዘንተ-አለም ተገዥነት ወደ ዜጋነት የማሸጋገር ተስፋውን እውን ሳናደርግ የምናርፍ አለመሆኑን የገባነው ቃላችንን በየአመቱ የምናድስበት እለት እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡ የምርጫ 97 ተአምር እንዲሳከ መስዋእትነት የከፈሉትን በሙሉ የምናስታውስበት፣ የእዚህን ምርጫ ድል አናስነጥቅም በማለት በዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የተጨፈጨፉትን፣ የታሰሩትን፣ ከስራቸው ከቀያቸው ተፈናቅለው በገዛ ሃገራቸውና በባእድ ምድሮች በስደት የሚንከራተቱትን የምንዘክርበት እለት ነው፡፡ ዛሬም የግንቦት 7ቱ ተአምር አቀጣጣዮች በመሆናቸው ብቻ በዘረኞች እስር ቤቶች ታጉረው ስቃያቸውን የሚያዩትን የፖለቲካና የህሊና እስረኞች በሙሉ አልረሳናችሁም የምንልበት እለት ነው፡፡

እንደ ንቅናቄ ድግሞ ይህ እለት የግንቦት7 ንቅናቄ ከተመሰረተ አንድ አመት የሞላው መሆኑን አባላቱ ደጋፊዎቹ የሚያስታውሱበት እለት፡፡ እውንም ንቅናቄያችን አንድ አመት ሞልቶታል፡፡ ንቅናቄያችን አንድ አመት ሞላው ብለን ግን፣ የቀንና የዘመን ቆጠራ በራሱ ግብ ይመስል ድግስ የምንደግስበት፣ የምንጨፍርበትና የምንፈነድቅበት በአል አይኖረንም፡፡ የተነሳነው ዘመን እየቆጠርን የራሳችንን ንቅናቄ የልደት በአል ለማክበር አይደለም፡፡ ንቅናቄያችንን ያቆምነው፣ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የጫነውን የብካይና የግፍ ቀንበር አንስተን የሃገራችንን ህዝብ የተሟሉ የዴሞክራሲ፣ የነጻነትና የእኩልነት መብቶቹ ተከብረው፣ አንድነቱን አጥብቆ በጋራ፣ በድህነት፣ በረሃብ፣ በድንቁርናና በበሽታ ላይ የሚረባረብበትን ሁኔታ በአስቸኳይ ለመፍጠር መሆኑን እናውቃለን፡፡ በመሆኑም፣ በዛሬው እለት የተመሰረትንበትን አንደኛ አመታችንን ስናከብር የምንጠይቀው ጥያቄዎች፣ ሃገራችንና ሁላችንም ከገባንበት አስፈሪና አሳፈሪ አጣብቂኝ አስከፊነት ጋር ሲነጻጻር ምን ሰርተናል? የግንቦት 7 1997 ህዝባዊ ራእይ ከግብ ለማድረስ እስካሁን የወሰድነው እርምጃ ከሚጠብቀን ረጅምና አሰቸጋሪ ጉዞ ጋር ስናወዳድረው ምን ያህል አጥጋቢ ነው? የሚሉ ይሆናሉ።

በአንድ አመት ውስጥ የግንቦት 7ንቅናቄ ብዙ ስራዎች ሰርቷል፡፡ በዋንኛነት ድርጅታዊ መሰረቱ ሃገር ቤት እንዲሆን በማድረግ፣ በውጭም ሃገር ሰፊ የአባላትና የደጋፊዎች መረብ በመዘርጋት ስራዎችን ሰርተናል፡፡ የወያኔን ፕሮፓጋንዳ በመመከት፣ ህዝብ የለውጥ ተስፋው እንዳይጨልም ቀላል የማይባሉ የህዝብ ግንኙነት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ አስቸጋሪ የሆነውን የወገናችንን በፖለቲካ ድርጅቶች መከፋትና ድርጅቶች ከእዚህ ወገናችን በሰበሰቡት ሃብት ላይ ባሳዩት ብክነት የተነሳ ገጥሞት የነበረውን የመለገስ ፍላጎት እጦት በመስበር የድርጅቱን የገንዘብ አቅም በማጠናከር የተወሰዱት እርምጃዎች የንቅናቄያችንን የፋይናንስ ነጻነት ማስከበር የቻሉ ሆነዋል፡፡ በፖለቲካ ባህል ደረጃ ዴሞክራሲ ጨዋነትና ስልጡንነት የተሞላበት የፖለቲካ መስክ መሆኑን በመረዳት፣ ባላንጣ አድርገው የሚያዩንና ጨዋነትና ስልጡንነት በሌለው መንገድ ሊቀርቡን የሚፈልጉትን ሳይቀሩ፣ በተራ ድርጅታዊ ስምና ክብር በተሞላ ግብዝነት ሳንታጀልና ራሳችንን ሳንስት በተቃዋሚ ጎራው መሃል ሌላው ቢቀር ሰላም እንዲወርድ የራሳችንን ጥረት አድርገናል፡፡ ትኩረታችንን በዋንኛው የሃገርና የህዝብ ጠላት በሆነው ዘረኛ አፋኝ በሆነው የወያኔ ቡድን ላይ ብቻ በማድርግ ተንቀሳቅሰናል፡፡ ሁኔታዎችና ወቅቱ የፈቀደውን ያህል መተባበር ከምንችላቸው ሃይሎች ጋር ለመተባበር የሚያስችሉንን ግልጽ ጉዳዮች ሳንሸፋፍን በአደባባይ በማቅረብ የወያኔን አምባገነናዊ ዘረኛት ለመመከት የሚችል ሰፊ የተቃዋሚዎች ህብረት እንዲፈጠር ጥረናል፡፡ ህብረቱ ባይፈጠር

እንኳን ለህብረቱ መፈጠር መነጋገር ከጀመርናቸው ሃይሎች ጋር በከፍተኛ የወገናዊ ስሜት መቀራረብ ችለናል፡፡ መተባበሩም የግዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የማይቀር መሆኑን ተረድተናል፡፡

ነገር ግን ከላይ የጠቀስናቸውና ሌሎችም ያልዘረዘርናቸው የንቅናቂያችን ክንውኖች ተባዝተው ቢከመሩ ጠቅላላ የሰራነው ስራ ሀገራችንና ሁላችንም ከምንገኝበት መከራ ለማውጣት መሰራት ከሚገባው ስራ ጋር ሲነጻጸር በውቂያኖስ መሃል እንደተጣለ ጠብታ ትንሽ መሆኑን አንክድም፡፡ ይህን የአንደኛ አመት በአል ስናስብ የንቅናቄያችን መሪዎች አባላትና ደጋፊዎች በእዚህ አንድ አመት ውስጥ ብዙ ሰርተናል ብለው የሚኮፈሱበት፣ ለአንድም ቀን ቢሆን ግዚያቸውን አመት ሞልቶናል በማለት ስራቸውን አቁመው በአል በማክበር ስም የሚፈንድቁበትና የሚኩራሩበት አድርገው እንዳያከበሩት የሚያደርገው ሃቅ ይህ ነው፡፡

ይህ ቀን ዘረኛ ከሆነው የመለስ ዜናዊ ግፈኛና ዘራፊ አገዛዝ ጋር ለሚደረገው ትግል ንቅናቄያችንም ሆነ ደጋፊዎቹ እንዲሁም ሰፊው የሃገሪቱ ህዝብ በሁሉም ረገድ መክፈል የሚገባውን መስዋእትነት የምናሰላበት፣ ለመስዋእትነት ቃልኪዳን የምንገባባት ቀን ነው፡፡ ንቅናቂያችን «ግንቦት 7 አንቺ እለት ብንረሳሽ የሚረሳ ይርሳን» ብሎ የትግሉን ማገፊያ፣ ስልጣንን ሳይሆን በግንቦት 1997 ህዝብ ያሳየውን ተአምር ዳግም መልሶ ማሳየት የሚችልበትን እድል አድርጎ የተነሳ ድርጅት ነው፡፡ ለንቅናቂያችን አባላት ከእዚህ በላይ ውበት ያለው፣ የሰብእና እርካታ የሚሰጥ ሃገራዊና ህዝባዊ ፕሮጀክት የለም፡፡ በሃገር ቤትም ይሁን በሃገር ውጭ የሚገኘው ሃገሩን የሚወድ ኢትዮጵያ ሁሉ፣ ህዝብ በምርጫ የመንግስት ስልጣንን ለመረጠው መስጠት የሚችልበትን ሁኔታ ከመፍጠር ሌላ ከፍተኛ የፖለቲካ ግብ እንደሌለው እናውቃለን፡፡

ስለእዚህ የንቅናቂያችንን መመስረት አንደኛ አመት አስበን በምንውልበት እለት ለወገኖቻችን የምናቀርበው የልደት በአል ድግስ ጥሪ የለንም፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ጥሪ «መጪው የትግል ወቅት የሚጠይቀውን ከባድና መራር ስራ ተባብረን በመስራት፣ ከገባንበት ሃገራዊና ህዝባዊ ፍዳና ውርደት በፍጥነት እንድንገላገል በእዚህ አንድ አመት ውስጥ ያሳየነውን መደጋገፍ የበለጠ አጠናክረን እንቀጥል» የሚል ነው፡፡

ይህን ካደረግን በእብሪት የተወጠረን የጥቂት ዘረኞች ብካይ አምራች፣ የግፍ አገዛዝ በአጭር ግዜ ውስጥ ከውድ ሃገራችን ውስጥ ጠራርገን  በማስወገድ፣ በቦታው የኢትዮጵያ ህዝብ ለነጻነቱ መከበር የከፈለውን መስዋእትነት የሚመጥንና ባለንበት አለምም የሰው ልጆች ስልጣኔ የደረሰበትን ከፍተኛ ደረጃ የሚያንጸባርቅ የፖለቲካ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ስርአት በሃገራችን መገንባት እንችላለን፡፡ የዛሬው እለት ጥሪያችን፣ «ኑ እንሰባሰብ፣ እንተባበር፣ ዘረኛትን አጨንግፍን በመቃብሩ ላይ አንድነትን፣ ፍቅርን፣ እኩልነትን፣ ፍትህንና ነጻነትን የሚያወድሰውን በአል እንደሚያዝያ 30 1997ቱ የሚሊዮኖች በአል በያስተሰርያል ዜማ ታጅበን በሀገራችን ምድር ለማክብር እንጣደፍ» ነው፡፡

ውድቀት የግንቦት 7ን ህዝባዊ ውብ ህልም ወደ ቅዠት ለቀየሩት ዘረኛ አምባገነኖች!
ድል በግንቦት 7 ህዝብ ያሳየውን ተአምር ለመድገም ታጥቀው ለተነሱ ወገኖች!
ግንቦት 7 ለፍትህ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ግንቦት 7 /2001 ዓ.ም